# ህግህ ለእግሬ መብራት

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት - ዘዳግም

አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት



ክፍል አንድ

ከአድኅኖ ተሾመ 1993 ዓ.ም

# ሕግህ ለእግሬ መብራት

ከአድነው ተሾመ

1993 ዓ.ም.

## የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት

ከዘፍጥረት እስከ ዘዳግም

(አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት)

## ክፍል አንድ

ይህንን መጽሐፍ ያ ደራሲው ፈቃድ በሙሉ
ወይም በከፊል ማባዛት ወይም መልሶ ማሳተም በሕግ
የተከለከለ ነው 1993 ዓ.ም

**Copyright 2001, Adnew Teshome**

# ምዕራፍ ስድስት

## ኦሪት ዘዳግም

ይህ መጽሐፍ የሙሴ አምስተኛው መጽሐፍ ሲሆን፣ ዘዳግም የተባለበትም ምክንያት ሙሴ ለአዲሱ ትውልድ አባቶቻቸው ከግብጽ ባርነት ወጥተው እንዴት እንደተጓዙና እግዚአብሔር ለአባቶቻቸው የሰጣቸውን ሕግ ለሁለተኛ ጊዜ ለአዲሱ ትውልድ ደግሞ ሲያሳስባቸው የሚያሳይ መጽሐፍ በመሆኑ ነው:: የዚህ መጽሐፍ ስም በእንግሊዘኛ "Deuteronomy" ሲሆን፣ ቃሉ የመጣው ከሁለት የግሪክ ቃሎች ነው:: እነዚህም ቃሎች (Deuteros) ሁለተኛ ማለት ሲሆን (Normos) ደግሞ (ሕግ) ማለት ነው:: በአንድነት ሲነበብ ለሁለተኛ ጊዜ የተሰጠ ሕግ ማለት ነው::

በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በጣም ጐልቶ የሚታየው ጥቅስ ወይም የመጽሐፉ ማዕከላዊ ጥቅስ፣ ኢየሱስ ከሕግ ሁሉ የሚበልጠው የመጀመሪያው ትእዛዝ ብሎ የጠራው ጥቅስ ነው::

ዘዳ. 6፥4-5 «እስራኤል ሆይ ስማ፤ አምላካችን እግዚአብሔር አንድ እግዚአብሔር ነው፤ አንተም አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ::»

በሥላሴ የማያምኑ ሰዎች፣ ይህ ጥቅስ የእግዚአብሔርን ሦስትነት አያሳይም ለማለት ይጠቀሙበታል፤ ነገር ግን በዚህ ጥቅስ ውስጥ በዕብራይስጥ «እግዚአብሔር» ለሚለው ቃል የሚጠቀመው «ኤሎሂም» የሚለዉ ቃል ሲሆን፣ ይህም የብዙ ቁጥር እንጂ የነጠላ ቁጥር አይደለም:: አንድነትን ብቻ ሳይሆን ብዙ ቁጥርንም የሚገልጽ ነው:: በተጨማሪም፣ «አንድ» ለሚለው ቃል የሚጠቀመው «ኢካድ» የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ሲሆን፣ይህ ቃል የሚያመለክተው ፍጹም አንድነትን ሳይሆን የኅብረት አንድነትን ነው::

## የዘዳግም መጽሐፍ በሁለት ይከፈላል::

፩፥ .ወደ ኋላ መመልከት (ምዕ. 1-11)

ሀ. ከሲና ጀምሮ የተጓዙትን ጉዞ (ምዕ. 1-3)
ለ. ከሲና የተሰጠውን ሕግ (ምዕ. 4-11)

፪÷ ወደፊት መመልከት (ምዕ. 12-34)
ሀ. ለአዲሱ ትውልድ የተሰጡ ማስጠንቀቂያዎችና ትእዛዞች (ምዕ. 12-30)
ለ. የሙሴ የመጨረሻ ቃላት፣ (ምዕ. 31-34)
- የሙሴ የመጨረሻ የማበረታቻና የማስጠንቀቂያ ቃል(ምዕ. 31)
- የሙሴ መዝሙር (ምዕ. 32)
- የሙሴ ባርኮት (ምዕ. 33)
- የሙሴ ሞት (ምዕ. 34)

ይህ መጽሐፍ አጉልቶ የሚያሳየው <u>የእግዚአብሔርን ታማኝነት</u> ነው።

ከዘዳ 6÷4-5 ሌላ በዚህ መጽሐፍ ጉልተው የሚታዩ ሁለት ጥቅሶች አሉ። አንደኛው፤ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ያደረገላቸውን ነገር ሁሉ አጠቃልሎ የሚገልጽ ሲሆን፣ ሁለተኛው ደግሞ እግዚአብሔር ከእሥራኤል የሚጠብቀው ምን እንደሆነ የሚገልጽ ነው።

ዘዳ. 6÷23 «ለአባቶቻችን ወደ ማለላቸው ምድር አግብቶ እርስዋን ይሰጠን ዘንድ ከዚያ (ከግብጽ) አወጣህ» ከዚህ ጥቅስ ሦስት ነገሮችን እናያለን፤

ሀ. ከግብጽ ባርነት አወጣን
ለ. ያወጣን ወደ ተስፋይቱ ምድር ሊያስገባን ነው፡ -
ሐ.ይህንንም ያደረገው ለአባቶቻችን (ለአብርሃም፣ ለይስሐቅና ለያዕቆብ) የሚለውን ቃል ሊያጸና ነው።

እግዚአብሔር ይህን ካደረገላቸው በኋላ ከእነርሱ የሚጠብቀው ምን እንደሆነ በዘዳ. 10፣12-13 ይናገራል። «እስራኤል ሆይ፣ አሁንስ አምላክህን እግዚአብሔርን ትፈራ ዘንድ በመንገዱም ሁሉ ትሄድ ዘንድ አምላክህንም እግዚአብሔርን ትወድድ ዘንድ በፍጹምም ልብህ በፍጹምም ነፍስህ ታመልከው ዘንድ መልካምም እንዲሆንልህ ዛሬ ለአንተ የማዝዘውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝና ሥርዓት ትጠብቅ ዘንድ ነው እንጂ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ የሚፈልገው ምንድር ነው?

እግዚአብሔር ለአብርሃም የገባውን ቃል ኪዳንና በሲና ተራራ ለእስራኤል የገባውን ቃል ኪዳን ልዩነት እንመልከት። ከዘዳ. ዘዳ.

6፥23 እንደምንረዳው፤ እግዚአብሔር እሥራኤላውያንን ለ40 ዓመታት ሁሉ ታግሦ፣ እነርሱ ባልታመኑበት ጊዜ እንኳን ቃል ኪዳኑን ጠብቆ ወደ ተስፋይቱ ምድር ያስገባቸው ለአብርሃም ስለገባው ቃል ኪዳን ነበረ።

እግዚአብሔር ከእስራኤላውያን ጋር በሙሴ አማካይነት በሲና ተራራ ቃል ኪዳን ቢገባም፤ እሥራኤላውያን እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር በሲና ተራራ ላይ የገባውን ቃል ኪዳን ሲያፈርሱ እንኳን ከአብርሃም ጋር ስለገባው ቃል ኪዳን ሲል ሲታገሳቸውና ወደ ምሕረቱና ወደ ርስታቸው ሲመልሳቸው እናያለን (ዘዳ. 9፥5፤ ዘሌ. 26፥41-42)።

ይህንን መጽሐፍ ሌላ ልዩ የሚያደርገው ነገር፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዲያብሎስ ሲፈተን ሦስቱንም ጊዜ ተጽፏል ብሎ የመለሰለት ከዚህ መጽሐፍ ነበር።

(ሉቃ. 4፣1-13፤ ማቴ. 4፥1-11)

- የመጀመሪያው ፈተና፤

«ኢየሱስም፣ ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ቃል ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ አይኖርም ተብሎ ተጽፎአል አለው»(ማቴ. 4፥4፤ ዘዳ. 8፥3)።

- ሁለተኛው ፈተና፤

«ኢየሱስም፣ ጌታን አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎአል አለው» (ማቴ. 4፥7፤ ዘዳ. 6፥16)።

- ሦስተኛው ፈተና፤

«... ለጌታህ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፎአል» (ማቴ. 4፥10፤ ዘዳ. 6፥13)።

በአጠቃላይ ይህ መጽሐፍ ለእግዚአብሔር ቃል ትልቅ ሥፍራና ትኩረት መስጠት እንዳለብን የሚያሳስብ መጽሐፍ ነው።

«እኔም ዛሬ አንተን የማዝዘውን ይህን ቃል በልብህ ያዝ። ለልጆችህም አስተምረው፣በቤትህም ስትቀመጥ፣ በመንገድም ስትሄድ፣ ስትተኛም፣ ስትነሳም ተጫወተው። በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፣ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ። በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው. (ዘዳ. 6፥6-9)።

ይህ መጽሐፍ በአጠቃላይ የሁለት ወራትን ድርጊቶች ያካተተ ሲሆን አንደኛው ወር ሙሴ ለአዲሱ ትውልድ፤ ያለፈውን ታሪክ፣ ለወደፊት መውሰድ ያለባቸውን ጥንቃቄና ያደረገላቸውን የመጨረሻ

ስንብት ሲያጠቃልል፤ ሁለተኛው ወር ደግሞ በመጨረሻው ምዕራፍ (ምዕ. 34) ሙሴ ከሞተ በኋላ እሥራኤላውያን ያለቀሱለትን 30 ቀናት ያጠቃልላል።

የዘዳግም መጽሐፍ የሚጀምረው ከግብጽ ከወጡ ከ40ኛው ዓመት ከአሥራ አንደኛው ወር ከመጀመሪያው ቀን እንደሆነ በዘዳ. 1፥3-4 እንረዳለን።

ሙሴ የሞተው እሥራኤላዊያን ከግብጽ በወጡ በ40ኛው ዓመት መጨረሻ ላይ እንደሆነ ከተለያዩ ሥፍራዎች መረዳት እንችላለን። በ40 ዓመቱ ወደ ሲና ምድረ በዳ ኮበለለ በ80 ዓመቱ የእግዚአብሔር ጥሪ መጣለት በ120 ዓመቱ ሞተ። ስለዚህ ዘዳግም ምዕ. 1 እስከ ምዕ. 33 የአንድ ወር ገለጻና የሙሴ መደምደሚያና ማስጠንቀቂያ ቃል ነው። ከዚያም በምዕ. 34 ሙሴ ሞቶ ለአንድ ወር ያለቅሱለታል።

<u>አምስቱን መጻሕፍት ከጊዜ አንጻር ስንመለከት፤</u>

| ዘፍጥረት | ዘጸዓት | ዘሌዋውያን | ዘኁልቍ | ዘዳግም |
|---|---|---|---|---|
| ከአዳም እስከ ዮሴፍ | ከዮሴፍ ሞት እስከ – ከግብጽ ባርነት ወጥተው ሁለት ዓመት ድረስ | ከሁለተኛው ዓመት መጀመሪያው ወር እስከ ሁለተኛው ወር (ዘኍ.1:1) | ከግብጽ ከወጡ ከ2 ዓመት ጀምሮ 40ው ዓመት እስኪያልቅ | ከ40ኛው ዓመት 11ኛው ወር እስከ 40ኛው ዓመት መጨረሻ |
| ከ2000 ዓመታት በላይ | ከ400 ዓመታት በላይ (ዘጸ.40:17 ሐዋ. 7:6) | የ1 ወር ጊዜ | 38 ዓመታት | 1ወር +1ወር ለሙሴ ለቅሶ =2ወር (ዘዳ.1:3–4) |

# ክፍል 1
# ወደ ኋላ መመልከት (ዘዳ. 1-12)

<u>ዘዳ. 1</u>፡ - ሙሴ ከሲና ተራራ ጀምሮ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ ያሳለፉትን ዘመን ይተርክላቸዋል።
«በሴይር ተራራ መንገድ ከኮሬብ እስከ ቃዴስ በርኔ ድረስ የአሥራ አንድ ቀን መንገድ ነው» (ቁ. 2)።

- የኮሬብ ተራራ የሲና ተራራ ነው፡ - እግዚአብሔር በዘጸ. 3 ላይ ለሙሴ በሚቃጠል ቁጥቋጦ የተገለጸውም በዚህ ተራራ ላይ ነው።

- ቃዴስ ደግሞ ወደ ተስፋይቱ ምድር ለመግባት ሰላዮች የተላኩበት ቦታ ነው።

    - የተስፋይቱ ምድር ምን ያህል ቅርብ እንደነበረች የሚያሳይ ጥቅስ ነው።

በቁ. 38 እግዚአብሔር ሙሴን «የነዌ ልጅ ኢያሱ እርሱ ወደዚያ ይገባል እርሱ ለእስራኤል ምድሪቱን ያወርሳልና <u>አደፋፍረው</u>» ይለዋል።

- እግዚአብሔር እስኪያደፋፍረን መጠበቅ ጥሩ ነው። እግዚአብሔር ሳዘጋጀልን ርስት ያደፋፍረናል። ከፍርሃት መጠንቀቅ እንዳለብን፣ ሁሉ ከአጉል ድፍረትም (ከሥጋ ድፍረት) መጠንቀቅ አለብን።

<u>ዘዳ.2</u>፤ ሙሴ ከቃዴስ በርኔ ለ 38 ዓመት የተንዙበትን ታሪክ ይተርካል። የሰልፈኞች ትውልድ (አሮጌው ትውልድ) ሁሉ ከሰፈሩ መካከል እስከ ጠፉ ድረስ ከቃዴስ በርኔ የተንዝንበት ሠላሳ ስምንት ዓመት ሆነ» (ቁ. 14)።

<u>ዘዳ.3</u>፤ አዲሱ ትውልድ በሁለቱ ነገሥታት (በዐግና በሴዎን) ላይ ስላገኙት ድልና ምድራቸውንም እንደወረሱ ይናገራል።

በዚህ ምዕራፍ እግዚአብሔር የሙሴን ልመና እንቢ ሲለው እናነባለን። እግዚአብሔር የማንንም ልመና እንቢ ለማለት መብቱ የተጠበቀ ነው። «እግዚአብሔር ግን በእናንተ ምክንያት ተቈጣኝ አልሰማኝም (ወደተስፋይቱ ምድር እንዲገባ የለመነውን ልመና)፤ እግዚአብሔር አለኝ፡ - <u>ይበቃሃል በዚህ ነገር ደግመህ አትናገረኝ</u>» (ቁ. 26)።

<u>ዘዳ.4</u> የእግዚአብሔርን ትእዛዝ እንዲጠብቁ ያስጠነቅቃቸዋል። (ከሲና ተራራ የተሰጣቸውን ትእዛዝ)

እግዚአብሔር አምላኩ የቀረበውና እንደዚህ ዓይነት የጽድቅ ሕግ ያለው ታላቅ ሕዝብ ማነው? በማለት ይጠይቃቸዋል (ቁ. 7-8)

ብዙ ጊዜ እኛም ከእግዚአብሔር የተነሣ የተቀበልነውን ሞገስና ታላቅነት አናውቅም (1ዮሐ. 3፥1)።

«ዓይኖችህ ያዩትን እንዳትረሳ ከልብህ እንዳይወድቅ ተጠንቀቅ፣ ነፍስህንም በትጋት ጠብቅ፣ ለልጆችህም ለልጅ ልጆችህም አስታውቀው. (ቁ. 10)። ከሁሉ በላይ መጠበቅ ያለብን ነፍሳችንን ነው።( ምሳ.4፥23) በቁ. 25-26 በእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሠራችሁ ጊዜ ከርስታችሁ ትጠፋላችሁ ይላቸዋል። ለዚህም ሰማይና ምድር ምስክሮች ናቸው ይላል።

በቁ. 30 ላይ ትንቢታዊ የሆነ ቃል ይናገራል። «በዘመኑ ፍጻሜ ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለህ» በማለት በአዲስ ኪዳን እሥራኤል በመጨረሻው ዘመን ኢየሱስ መሲህ መሆኑን አውቀው እንደሚመለሱ የሚናገረውን ይተነብያል (ሮሜ 11፥25-31)።

ዘዳ.5፣ አሥርቱ ቃላትን በድጋሚ ይዘረዝራል። በተጨማሪም እሥራኤላውያን እግዚአብሔር በሲና ተራራ ላይ በእሳት ተገልጦ አሥርቱ ቃላትን ሲሰጥ እጅግ እንደፈሩና የእግዚአብሔርን ድምጽ ደግመን ብንሰማ እንሞታለን አንተ ተናገረን፤ እግዚአብሔር አይናገረን ብለው በእግዚአብሔር ፍርሃት እንደተዋጡ ይነግረናል። በዚህ ሁኔታ ላይ እያሉ እግዚአብሔር ለሙሴ፤ «ለእነርሱ ለዘላለምም ለልጆቻቸው መልካም ይሆንላቸው ዘንድ እንዲፈሩኝ ሁልጊዜም ትእዛዜን ሁሉ እንዲጠብቁ እንዲህ ያለ ልብ ምነው በሆነላቸው»(ቁ. 29) ይለዋል። ይህ ልብ ከእነርሱ ጋር ብዙ እንዳልቆየ ከታሪካቸው እንረዳለን። ከ40 ቀናት በኋላ የወርቅ ጥጃ ሠርተው አመለኩ ከእግዚብሔርም ራቁ።

ዘዳ.6፡ - ይህ ምዕራፍ ኢየሱስ ፊተኛዩቱ ትእዛዝ ያላት ትእዛዝ ያለችበት ምዕራፍ ነው። «አምላክህን እግዚአብሔርን በፍጹም ልብህ፤ በፍጹም ነፍስህ በፍጹምም ኃይልህ ውደድ» (ቁ.5)። በተጨማሪም፤ በዚህ ምዕራፍ ቀደም ብለን የተመለከትናቸውን ስለ እግዚአብሔር ቃል ለእሥራኤላውያን የተሰጠውን ልዩ የሆነ ጥብቅ ማሳሰቢያ ከ6-9 እናገኛለን።

እንዲሁም ኢየሱስ ሲፈተን የጠቀሳቸው ሁለት ጥቅሶች ከዚህ ምዕራፍ እንደሆነ አይተናል( ቁ. 13 እና 16)።

ዘዳ. 7፡ - ሊጠብቁት የሚገባቸውን ትእዛዞች መንገርናማስጠንቀቅ ይቀጥላል።

በዚህ ምዕራፍ አንድ ለየት ያለ ነገር የምናየው፤ ትእዛዙንና ፍርዱን ብትጠብቃት ብታደርጋትም፤ «እግዚአብሔርም ሕማምን ሁሉ ከአንተ ያርቃል የምታውቀውንም ክፉውን የግብጽ በሽታ ሁሉ በአንተ ላይ አያደርስብህም» (ቁ.15) የሚል የተስፋ ቃል ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን እንኳን፣ የእግዚብሔር ሕዝብ ከበሽታ ነፃ ሆኖ ይኖር ዘንድ እንዴት አብልጦ ከበሽታ ሁሉ አይጠብቀንም፡፡ በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ ክርስቶስ ከደዌና ከበሽታ ነፃ ሊያወጣን ጀርባው እንቆሰለልን ይናገራል፡፡ «በመገረፉ ቁስል ተፈውሳችሁ» (1ጴጥ. 2÷24)፡፡

ዘዳ.8፤ እግዚአብሔር ለ40 ዓመታት በምድረ በዳ የመራቸው በልባቸው ያለውን ትእዛዝ ይጠብቁ ወይም አይጠብቁ እንደሆነ ለማወቅ እንደነበረ ይገልጻል፡፡ «ሰው ከእግዚአብሔር አፍ በሚወጣ ነገር ሁሉ እንጂ በእንጀራ ብቻ በሕይወት እንዳይኖር ያስታውቅህ ዘንድ አስጨነቀህ አስራብህም፣ አንተም ያላወቅኸውን አባቶችም ያላወቁትን መና አበላህ»(ቁ.3)፡፡ በማለት፣ እግዚብሔር አንዳንድ ጊዜ አንዳንድ ነገሮችነ ሊያስተምረን በጭንቀት፣ በረሃብ፣ በፈተና ውስጥ እንደሚያሳልፈን ይናገራል፡፡

«ጻድቅ ሲራብ ዘሩም እህልን ሲለምን አላየሁም» የሚለውን ጥቅስ ብቻ ይዘን አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር በረሃብና በጭንቀት ውስጥ እንድናልፍ እንደሚፈቅድም መዘንጋት የለብንም፡፡

* ጻድቅ ሲራብና ሲለምን አላየሁም፤ ያለው ዳዊት፤ በሌላ ቦታ «ሥርዓትህን እማር ዘንድ ያስጨነቀኝ ለመልካም ሆነልኝ» ይላል፡፡

እግዚአብሔር እሥራኤልን ለጥቂት ጊዜ ቢያስጨንቅና ቢያስርብም፣ ጥበቃውና እንክብካቤው ዘወትር ከእነርሱ ጋር ነበረ፡፡ ፣በእነዚህ አርባ ዓመታት የለበስከው ልብስ አላረጀም እግርህም አላበጠም፡፡ ሰውም ልጁን እንደሚገሥጽ እንዲሁም እግዚአብሔር አንተን እንዲገሥጽ በልብህ አስተውል» ይላቸዋል( ቁ.4)፡፡

በቁ.12 ላይ ወደ ተስፋይቱ ምድር ገብተው ከወረሱ በኋላ እግዚአብሔርን እንዳይረሱ ያስጠነቅቃቸዋል፡፡ «ከበላህና ከጠገብክ በኋላ መልካምም ቤት ሠርተህ ከተቀመጥህበት በኋላ የላምና የበግ መንጋ ከበዛልህ በኋላ፣ ብርህና ወርቅህም ያለህም ሁሉ ከበዛልህ በኋላ ልብህ እንዳይጓደድ» (እንዳይታበይ ማለት ነው)፡፡

እግዚአብሔር በመከራና በጭንቀትያሳለፋቸው፤ «በመጨረሻው ዘመን መልካም ያደርግልህ ዘንድ» ነው በማለት ይነግራቸዋል (ቁ. 16)፡፡ የእግዚአብሔር ነገር ሁልጊዜ መጨረሻው መልካም ነው፡፡

የሰይጣንና የዓለም ነገር ግን መጀመሪያው ጣፋጭ መጨረሻው መራራ ነው (ዕብ. 11÷25)።

«በልብህም፡ - ጉልበቴ የእጄም ብርታት ይህን ሀብት አመጣልኝ እንዳትል። ነገር ግን ዛሬ እንደሆነ ለአባቶችህ የማለውን ቃል ኪዳን ያጸና ዘንድ፣ ሀብት ለማከማቸት እርሱ ጉልበት ሰጥቶሃልና አምላክህን እግዚአብሔርን አስብ» (ቁ. 17ና 18)።

ከዚህ ጥቅስ የምንረዳው በምድር ላይ ሀብት ቢበዛልን፡ -

1ኛ. ሀብት ያገኘንበትን ጉልበት የሰጠን እግዚአብሔር እንደሆነ፤
2ኛ. ሀብት እንድናከማች ያደረገበት ዋና ዓላማ «ቃል ኪዳኑን በምድር ላይ ለማጽናት» እንደሆነ ነው።

በአሁኑ ዘመን በምድር ላይ እግዚአብሔር ሊያጸና የሚፈልገው ዋና ቃል ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ ደም በኩል የገባልን የአዲስ ኪዳን ወንጌል ነው። በሌላ አነጋገር፣ ሀብት ቢበዛልን እኛ ራሳችንን እንድንንደላቀቅበት ሳይሆን የክርስቶስ ወንጌል እንዲስፋፋበት፣ ነፍሳቶች እንዲድኑበት ነው።

ለግል ሕይወታችን ስለሚያስፈልገን ነገር ሲናገር፡ – 1ጢሞ. 6÷1-8 «ኑሮዬ ይበቃኛል ለሚለው ግን እግዚአብሔርን መምሰል እጅግ ማትረፊያ ነው። ወደ ዓለም ምንም እንኳ አላመጣንምና፣ አንዳችንም ልንወስድ አይቻለንም። ምግብና ልብስ ከኖረን ግን እርሱ ይበቃናል።» ይላል።

ዘዳ. 9፡ - እግዚአብሔር ወደ ተስፋይቱ ምድር የሚያስገባቸው ስለ ጽድቃቸው እንዳልሆነ ይነግራቸዋል።

«ምድራቸውን ትወርሳት ዘንድ የምትገባው ስለ ጽድቅህና ስለ ልብህ ቅንነት አይደለም፤ ለአባቶችህ ለአብርሃምና ለይስሐቅ ለያቆብም የማለላቸውን ቃል ይፈጽም ዘንድ ነው። እንግዲህ አንተ አንገተ ደንዳና ሕዝብ ነህና አምላክህ እግዚአብሔር ይህችን መልካም ምድር ርስት አድርጎ የሰጠህ ስለ ጽድቅህ እንዳይደለ እወቅ» (ቁ.5-6)፡ ፡

በአጠቃላይ፤ እግዚአብሔር አንድ መልካም ነገር ሲያደርግልን ወይም በእኛ በኩል አንድ መልካም ነገር ሲያደርግ በጽድቃችን እንዳይመስለን ያስጠነቅቀናል። የእግዚብሔርን ፈቃድ ካደረግህ በኋላ፤

«እኛ የማንጠቅም ባሪያዎች የሚገባንን አደረግን» በሉ ነው የተባልነው።

<u>ዘዳ.10</u>- ከእግዚአብሔር ጋር እንዲጣበቁ ይነግራቸዋል።

«አምላክህን እግዚአብሔርን ፍራ፣ እርሱንም አምልክ፣ ከእርሱም ተጣበቅ፤ በስሙም ማል ... <u>እርሱ ክብርህ</u> ነው፣ እርሱም አምላክህ ነው»(ቁ.20-21)። እግዚአብሔር እራሱ <u>ክብራችን</u> ነው።

<u>ዘዳ. 11</u>፡ - የእግዚአብሔርን ቀል ከጠበቁና ካደረጉ ማንም በፊታቸው መቆም እንደማይችልና የረገጡት ምድር ሁሉ ለእነርሱ እንደሚሆን ይነግራቸዋል።

«በእናንተም ፊት ማንም መቆም አይችልም፤ አምላካችሁ እግዚአብሔር ... ማስፈራታችሁን ማስደንገጣችሁንም በምትረግጡአት ምድር ሁሉ ላይ ያኖራል. (ቁ. 25)።

# ክፍል ሁለት

## ወደ ፊት መመልከት፡ - ዘዳ. 12 - 34

<u>ዘዳ.12</u>፡ - ለእግዚአብሔር አሥራታቸውን፣ በኩራታቸውን፣ ስእለታቸውንና በፈቃዳቸው የሚያቀርቡትን መሥዋዕት ሁሉ እግዚአብሔር በመረጠው ሥፍራ ማቅረብ እንዳለባቸው ያሳስባቸዋል።

<u>በዚህ ምዕራፍ ሦስት ጊዜ ደስ ይበላችሁ የሚል ቃል እናነባለን፤</u>

ቁ. 7 «አምላክህ እግዚአብሔር በባረከህ ነገር ሁሉ እናንተና ቤተሰባችሁ ደስ ይበላችሁ።»

ቁ. 12 « ... በአምላካችሁ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበላችሁ።»

ቁ. 18 «... እጅህንም በምትዘረጋበት ነገር ሁሉ በአምላክህ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይበልህ።»

ከዚህ ምዕራፍ የምንማረው፤ እውነተኛ መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በሚቀርብበት ቦታ ሁልጊዜ እውነተኛ ደስታ አለ።

<u>ዘዳ. 13</u>፡ - ባዕድ አምልኮ ከመካከላቸው እንዲወገድ ያሳብባል።

ቁ. 1-5 - <u>አንድ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ</u> ቢነሣ ምልክትም ተአምራትም ቢሰጥህ እንደ ነገረህም <u>ምልክቱ ተአምራቱም ቢፈጸም</u> እርሱም ሄደን የማታውቃቸውን <u>ሌሎች አማልክት እንከተል እናምልካቸውም ቢልህ</u> አምላካችሁን እግዚአብሔርን በፍጹም ልባችሁ በፍጹምም ነፍሳችሁ ትወዱት እንደሆነ ያውቅ ዘንድ አምላካችሁ እግዚአብሔር ሊፈትናችሁ ነውና የዚያን ነቢይ ቃል ወይም ያን ሕልም አላሚ አትስማ፡፡ ... <u>ያ ነቢይ ወይም ሕልም አላሚ ይገደል</u>፤ እንዲሁም ክፉውን ነገር ከመካከልህ አርቅ፡፡»

<u>ቁ.6-11</u> እንደዚሁ፤ ዘመድ ሚስት፣ ወዳጅ ሊያሳስትህ ቢሞክር ይገደል፡ - «እርሱን ከመግደል በፊት የአንተ እጅ ከዚያም በኋላ የሕዝቡ ሁሉ እጅ በላዩ ትሁን፡፡» እግዚአብሔር ከቤተሰብ፣ ከትዳር ከወዳጅ ሁሉ በላይ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ቁ.12-18፡ - አንድ ከተማ በሙሉ ቢስት፤ ከተማውን በከተማውም ያለውን ሁሉ አጥፋ «ከተማይቱንም ዕቃዋንም ሁሉ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር በእሳት ፈጽመህ ታቃጥላለህ፣ ለዘላለም ወና ትሆናለች፡፡ ... እርም ከሆነው አንዳች ነገር በእጅህ አይንጠልጠልብህ፡፡»

<u>ዘዳ.14</u>፡ - ስለ ሞተ ሰው ራሳቸውን እንዳይነጩና እንዳይላጩ እንዲሁም የሚበሏቸውና የማይበሏቸው እንስሳት የትኞቹ እንደሆኑ ይነግራቸዋል፡፡

ይህንን ጥንቃቄ ለምን እንደሚያደርጉ ሲናገር፤ «እናንተ የአምላካችሁ የእግዚአብሔር ልጆች ናችሁ ለአምላክህ ለእግዚአብሔር አንተ ቅዱስ ሕዝብ ነህና ...» ይላል (ቁ. 1-2)፡፡

ከቁ.22-29 አሥራትና በኩራት ማቅረብ እንዳለባቸው ይነግራቸዋል፡፡
<u>ዘዳ. 15</u>፡ - በየሰባት ዓመት የዕዳ ምህረት እንዲያደርጉ ይናገራል፡፡

- ማንኛውም ሰው በሰባተኛው ዓመት በወንድሙ ላይ ያለውን ዕዳ ይተዋል፡፡
- ይህንን ትእዛዝ ቢፈጽሙ ምን እንደሚሆን ይነግራቸዋል፡፡

ቁ.5 «የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽመህ ብትሰማ ታደርጋትም ዘንድ ዛሬ የማዝህን <u>ይህችን ትእዛዝ ሁሉ ብትጠብቅ በመካከልህ ድሀ አይኖርም</u>፡፡» በዓለም ውስጥ ያለው ድህነት ሰው

ስራሽ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ ብዙ ጊዜ ሰዎች፤ እግዚአብሔር ካለና ለሰው ግድ ካለው ለምን ይኼ ሁሉ ደህነት ረሃብ ጦርነት ወዘተ… ይኖራል? ይላሉ ፡፡ ከነዚህ ጥቅስ እንደምናየው ሚሉ የሰው ልጅ የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ቢከተል ኖሮ በዓለም ወስጥ የምናየው ደህነት ረሃብ ጦርነት ወዘተ…ባልኖረ ነበር፡፡

የእግዚአብሔርን ቃል በምሳሌ 19፡3‹‹የሰው ስንፍና መንገዱን ታጣምማበታለች ልቡም በእግዚአብሔርን ላይ ይቆጣል››በማለት የሰው ልጅ በራሱ ስንፍና በግል ሕይወቱም ሆነ በዓለም ላይ ባመጣው ቀወስ በእግዚአብሔርን ላይ እንደሚቆጣ አስቀድሞ ተናግሯል፡፡

በተጨማሪም፤ ከቁ. 7-11 ለድሃ መለገስ እንዳለብንና <u>ስስት ኃጢአት እንደሆነ</u> ይገልጻል፡፡ «ከወንድሞችህ አንዱ ቢደኽይ ልብህን አታጽና በደሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ … ወደ እግዚአብሐር እንዳይጮኽ ኃጢአትም እንዳይሆንብህ ተጠንቀቅ፡፡ … በሰጠኸውም ጊዜ ልብህ አይጸጸት፡፡»

ቁ.12-18፡ - «ወንድምህን ዕብራዊውን ወይም ዕብራዊቱን ብትገዛ፣ ስድስት ዓመት ያገለግሉህ በሰባተኛውም ዓመት ከአንተ ዘንድ አርነት አውጣው፡፡ … <u>እርሱ ግን አንተንና ቤትህን ስለ ወደደ</u> ከአንተም ጋር መልካም ሰለሆነለት፡ - ልወጣ አልወድም ቢል አንተ ወስፌ ወስደህ በቤትህ በር ላይ ጆሮውን ትበሳዋለህ ለዘላለምም ባሪያ ይሆንልሃል፡፡» ይህ ሁኔታ እግዚአብሔር የባርነትን ስርዓት ይደግፋል ማለት ሳይሆን የውዴታና የፍቅር ባርነትን ነው የሚያሳየው፡፡ እኛም ጌታ ኢየሱስንና ቤቱን ስለወደድን ለዘላለም ባሪያ ሆነንለታል፡፡

<u>ዘዳ.16</u>፡ - ስለ ሦስቱ ዓመታዊ የፌስታ በዓላት ይናገራል፡፡

1. የፋሲካ የቂጣ በዓል ቁ. 1-8
2. የሰባቱ ሱባዔ( በዓለ ኃምሳ) በዓል ቁ. 9-12
3. የዳስ በዓል ፡ - ቁ. 13-17

እነዚህ ሦስቱ በዓላት በዘሌ 23 ከተጠቀሱት አምስት ዓመታዊ በዓላት ውስጥ ሕዝቡ በመብላትና በመጠጣት (በእግዚአብሔር ፊት) ደስ የሚሰኙባቸው በዓላት ናቸው፡፡ ያልተጠቀሱት ሁለት ዓመታዊ በዓላት የመለከት ድምፅ በዓል (በሰባተኛው ወር በጀመሪያውን ቀን) እና የማስተሰርያው ቀን በዓል (በሰባተኛው ወር በ10ኛው ቀን የሚውሉት) የሚውሉት ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለቱ በዓላት እንደ ሦስቱ የፌስታ በዓላት አይደሉም፡፡

ቁ. 16 በእነዚህ በሦስቱ በዓላት «በእግዚአብሔርም ፊት ባዶ እጃቸውን አይታዩ» ይላል፡፡

ቁ.18-20 ቅን ፍርድን ስለ መፍረድ ይናገራል፡፡ «ፍርድን አታጣም፣ ፊት አይተህም አታድላ፤ ጉቦ የጥበበኞችን ዓይን ያሳውራል፣ የጻድቃንንም ቃል ያጣምማልና፣ ጉቦ አትቀበል፡፡»

<u>ዘዳ.17፡</u> - ተጨማሪ ማስጠንቀቂያዎችና ትእዛዞች፡፡

ቁ. 12፡ - እግዚአብሔር የሾማቸውን መሪያዎች ስለማክበር «ማናቸውም ሰው ቢኰራ በዚያም አምላክህን እግዚአብሔርን ለማገልገል የሚቆመውን ካህኑን ወይም ፈራጁን ለመስማት ባይወደድ፣ ያ ሰው ይሙት ከእስራኤልም ዘንድ ክፉትን አስወግድ፣ ሕዝቡም ሁሉ ሰምቶ ይፈራል፣ ከዚያም ወዲያ አይኰራም፡፡»

ከቁ. 14-20፡ - <u>ንጉሥ በሚያነግሡበት ጊዜ መመሪያ፤</u>
«... ወንድምህ ያልሆነውን ከሌላ ወገን ሰው በላይ ንጉሥ ታደርግ ዘንድ አይገባህም፡፡»

በዚህ ክፍል ውስጥ አንድ መሪ ሊያደርጋቸው የሚገባቸውን መሠረታዊ ጥንቃቄዎች ይነግረናል፡፡ ለመንፈሳዊም መሪ የሚጠቅም መመሪያ ነው፡፡

ነገር ግን ንጉሡ ለራሱ፡ -

1. <u>ፈረሶችን አያበዛም</u> -
   ፈረሶችን አያበዛም ሲል፡ - ኃይልንና ሥልጣንን ያመለክታል፡፡ በኃይሉና በሥልጣኑ እንዳይመካና ሕዝቡንም እንዳያስጨንቅ፡፡
   ዳዊት በመዝ. 19 (20)፣ 7-9 «እነዚህ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን» ያለው ይህ ማስጠንቀቂያ ስለገባው ነው፡፡

2. <u>ሚስቶችን ለእርሱ አያበዛም፡ -</u>

ከሥጋዊ ምኞት መቆጠብ እንዳለበት፡፡ የእግዚአብሔር ቃል በምሳሌ 16፣32 «ከተማን ከሚገዛ ይልቅ ራሱን የሚገዛ ይበልጣል» የሚለው ለዚህ ነው፡፡

በነገ. 11፥1-8 ንጉሡ ሰለሞን በሚስቶች ብዛትና በሥጋዊ ምኞት እንደ ወደቀ እናነባለን፡፡ ስሜቱንና ሥጋዊ ምኞቱን ካልገዛ ሕዝብን መግዛት እንዴት ይችላል?

3. <u>ወርቅና ብርም ለእርሱ እጅግ አያበዛም</u>፡ -

ገንዘብን መውደድ የኃጢአት ሁሉ ሥር ነውና በገንዘብ ፍቅር እንዳይታለል ወርቅና ብርም አያበዛም፡፡

4. <u>የእግዚአብሔርን ሕግ ለራሱ በመጽሐፍ አጽፎ ዕድሜውን ሁሉ ያንብበው</u>፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት ሦስት ነገሮች መራቅ ብቻ ሳይሆን ወደ እግዚአብሔር ሕግ መቅረብ አለበት፡፡

አንድ መሪ፤ ከሥልጣን ጥማት፣ ከሥጋዊ ምኞትና ከገንዘብ ፍቅር ከራቀና የእግዚአብሔርን ቃል መመሪያው ካደረገ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ሙሉ በሙሉ መፈጸም ይችላል፡፡ ዳዊት ይህንን ነው ያደረገው፡፡ «ዳዊትም በራሱ ዘመን የእግዚአብሔርን አሳብ ካገለገለ በኋላ አንቀላፋ» (ሐዋ. 13፥36)፡፡ እነዚህን ትእዛዞች በተላለፈው መጠን ደግሞ ዋጋ ከፍሏል፡፡
<u>ዘዳ. 18፡</u> - ስለ ምዋርትና አስማት፤ ስለ ሐሰተኛ ነቢይ ይናገራል፡፡

ቁ. 10 «ወንድ ልጁን ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ ምዋርተኛም፣ ሞራ ገላጭም፣ አስማተኛም፣ መተተኛም፣ በድግምት የሚጠነቁልም፣ መናፍስትንም የሚጠራ፣ ጠንቋይም፣ ሙታን ሳቢም በአንተ ዘንድ አይገኝ፡፡ ይህንም የሚያደርግ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የተጠላ ነው፡፡»

በቁ. 16 ላይ «አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ መካከል ከወንድሞችህ እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሣልሃል፣ እርሱንም ታደምጣለህ፡፡» በማለት ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ትንቢታዊ የሆነን ቃል ከተናገረ በኋላ በቁ.20-22 ነቢይ ነኝ ለሚል ሰው ሁሉ ማስጠንቀቂያን ይሰጣቸዋል «ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝኩትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ እርሱ ይገደል፡፡ በልብህም፣ እግዚአብሔር ያልተናገረውን ቃል እናውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለናል? ብትል ነቢዩ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ የተናገረው ነገር ባይሆን ባይመጣም፣ ያ ነገር እግዚአብሔር ያልተናገረው ነው፤ ነቢዩ፣ በድፍረቱ ተናግሮታል እርሱን አትፍራው፡፡»

<u>ዘዳ. 19</u>፡ - ስለ መማጸኛ ከተሞችና ስለ ሐሰት ምስክር ይናገራል።

ቁ. 18 «ፈራጆቹም አጥብቀው ይመረምራሉ፣ ያም ምስክር ሐሰተኛ ምስክር ሆኖ በወንድሙ ላይ በሐሰት ተናግሮ ቢገኝ በወንድሙ ላይ ያደርገው ዘንድ ያሰበውን፣ በእርሱ ላይ ትመልሱበታላችሁ።»

<u>ዘዳ. 20</u>፡ - ጠላቶቻቸውን ለመውጋት በሚወጡበት ጊዜ መመሪያ

ይህ ምዕራፍ በአጭሩ የሚናገረው፡ -

<u>ጠላቶችህን ለመውጋት በወጣህ ጊዜ</u>፡ -

1. አምላክህ ከአንተ ጋር ነውና አትፍራቸው
2. ካህኑ ተነሥቶ ሕዝቡን በእግዚአብሔር ቃል ያበረታታል (ይህ ቃል፣ መንፈሳዊ መሪዎች በጽድቅ ላይ በተመሠረተ ጦርነት ላይ ሚና እንዳላቸው ያሳስበናል)
3. አለቆች ለሕዝቡ እንዲህ ይላሉ፤

ሀ. አዲስ ቤት ሠርቶ ያላስመረቀ ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ሌላም ሰው እንዳያስመርቀው ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ።

ለ. ወይን ተክሎ ፍሬውን ያልበላ ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ሌላም ሰው ፍሬውን እንዳይበላ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ።

ሐ. ሚስት አጭቶ ያላገባት ሰው ቢኖር በሰልፍ እንዳይሞት ሌላም ሰው እንዳያገባት ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ።

መ. ማንም ፈሪና ድንጉጥ ሰው ቢሆን እርሱ ፈርቶ የወንድሞቹን ልብ ደግሞ እንዳያስፈራ ወደ ቤቱ ተመልሶ ይሂድ።

ከእነዚህ መመሪያዎች የምናስተውለው አንድ ነገር ቢኖር፤ አንድ ሰው ያልተቋጨ ወይም ያላለቀ ጉዳይ ኖሮት እንዲሞት የእግዚአብሔር ፈቃድ እንዳልሆነ ነው። እግዚአብሔር ንጉሡን ሕዝቅያስን «የምትሞትበት ቀን ደርሶአልና ቤትህን አዘጋጅ» ብሎ ያስጠነቀቀው ለዚህ ነበረ። ቤታችንን ሳናዘጋጅ እንድንሰናበት የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም።

- «እርሱ ፈርቶ የወንድሞቹን ልብ ደግሞ እንዳያስፈራ» የሚለው ማሳሰቢያ፣ ፍርሃት እንደ ተስቦ በሽታ የሚተላለፍ እንደሆነ ያሳየናል፡፡

ከቁ. 10-20 ፡ - <u>አንዲትን ከተማ ሊወጉ ሲወጡ መመሪያ፤</u>

1. አስቀድመህ በዕርቅ ቃል ጥራቸው
2. የዕርቅ ቃል ቢመልሱልህ፣ ይገብሩልህ፣ ያገልግሉህም
3. ዕርቅ ባይፈልጉና ሊዋጉ ቢወድዱ

   ሀ. ከተማይቱን ትከባለህ ታስጨንቃትማለህ
   ለ. በእርስዋ ያሉትን ወንዶች ሁሉ በሰይፍ ትገድላለህ
   ሐ. ሴቶቹን ሕፃናትና፣ እንስሶችን በከተማይቱ ያለውን ሁሉ ለአንተ ትወስዳለህ፡፡

4. በከበብካት ጊዜ ከእነርሱ ትበላለህና ዛፎችዋን አትቁረጥ፡፡

<u>ከዘዳ. 21-25</u> ልዩ ልዩ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ትእዛዞችንና መመሪያዎችን ያስተላልፋል፡፡

በዘዳ. 21፥1-9 አንድ ሰው በሜዳ ሞቶ ቢገኝ ሊደረግ የሚገባው ሥርዓት ይናገራል፡፡ «... ወደ ተገደለው ሰው አቅራቢያ የሆናችው የከተማይቱ ሽማግሌዎች ሁሉ በሸለቆው ውስጥ አንገትዋ በተሰበረው ጊደር ላይ እጃቸውን ሲታጠቡ፡ - እጃችን ይህን ደም አላፈሰሰችም፤ ዓይናችንም አላየችም፣ አቤቱ የተቤዠኸውን ሕዝብህን እስራኤልን ይቅር በል፣ በሕዝብህም በእስራኤል ላይ የንጹሕን ደም በደል አትቁጠር ብለው ይናገራሉ፡፡ ስለ ደሙም ይሰረይላቸዋል፡፡»

ዘዳ. 21፥10-21 ለአባቱና ለእናቱ የማይታዘዝ ዓመጸኛ ልጅ ስለሚደርስበት ፍርድ ይናገራል፡፡ «... አባቱና እናቱ ይዘው ወደ ከተማው ሽማግሌዎች ... ያምጡት፤ የከተማውንም ሽማግሌዎች፣ ይህ ልጃችን እልከኛና ዓመጸኛ ነው ለቃላችንም አይታዘዝም ስስታምና ሰካራም ነው ይበሉአቸው፡፡ የከተማውም ሰዎች ሁሉ እስኪሞት ድረስ በድንጋይ ይውገሩት፡፡»

ዘዳ. 21፥22-28 እንጨት ላይ የተሰቀለ ሁሉ በእግዚአብሔር ዘንድ የተረገመ እንደሆነ ይናገራል፡፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል እርግማን እንደሆነልን በገላ. 3፣13 እናነባለን፡፡ «በእንጨት

የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው፤ ተብሎ ተጽፎአልና፣ ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን፡፡»

<u>ዘዳ. 22 - ልዩ ልዩ ማኅበራዊ የሆኑ ትእዛዞች</u>

ቁ. 1-12 . የተለያዩ ማሳሰቢያዎች

- የሌላው ንብረት ጠባቂ እንደሆኑ
- በሴትና በወንድ መካከል የአለባበስ ልዩነት እንዲኖር
- ለእንስሳት ርኅራኄ እንዲያሳዩ
- ቤት ሲሠሩ በጥንቃቄ እንዲሠሩ
- ስለ እርሻና ስለ ልብስ የተሰጠ ማሳሰቢያ

ቁ. 13-30

- ስለ ጋብቻና ትዳር፣ እንዲሁም ታማኝ ሆኖ ያልተገኘ ሰው ስለሚደርስበት ፍርድ
- ድንግልና ያልተገኘባት ልጃገረድ በድንጋይ ተወግራ እንደምትሞት
- በምንዝርና የተገኘ ሰው እንደሚገደል

<u>ዘዳ. 23-ልዩ ልዩ ትእዛዛት</u>

ቁ. 1-8፤ ማን ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ መግባት እንደሌለበት

- ጃንደረባና ዲቃላ፣
- አሞናዊና ሞዓባዊ( በመንገድ ላይ አልተቀበሏችሁምና)
- ኤዶማዊና (የኤሳው ዘር) ግብፃዊ ከሦስተኛው ትውልድ ጀምሮ መግባት ይችላል፡፡ «ኤዶማዊው ወንድምህ ነውና፣ አትጸየፈው፤ ግብፃዊውንም በአገሩ ስደተኛ ነበርና አትጸየፈው፡፡ ከእነርሱም በሦስተኛው ትውልድ የሚወለዱ ልጆች ወደ እግዚአብሔር ጉባኤ ይግቡ» (ቁ. 8)፡፡

ቁ.9 «ጠላቶችህን ልትወጋ በወጣህ ጊዜ <u>ከክፉ ነገር ሁሉ ሰውነትህን ጠብቅ</u>»

- በጠላታችን ላይ ድል ከማግኘታችን በፊት በራሳችን (በሥጋችን) ላይ ድል ማግኘት አለብን፡፡ የውስጡን ውጊያ ሳናሸንፍ የውጩን ውጊያ ማሸነፍ አንችልም፡፡

ቁ. 10-14 ሰውነትንና ሰፈርን በንጽህና ስለመጠበቅ «… ወደ ሜዳም ትወጣበት ዘንድ ከሰፈር ውጭ ቦታ ይሁልንህ፡፡ ከመሣሪያህም ጋር መቆፈሪያ ያዝ በሜዳም በተቀመጥህ ጊዜ ትምስበታለህ፣ ዞረህም ከአንተ የወጣውን በአፈር ትከድነዋለህ፡፡ አምላክህ እግዚአብሔር ሊያድንህ ጠላቶችህንም በእጅህ አሳልፎ ሊሰጥህ <u>በሰፈርህ መካከል ይሄዳልና ስለዚህ ነውረኛ ነገር እንዳያይብህ ፊቱንም ከአንተ እንዳይመልስ ሰፈርህ የተቀደሰ ይሁን</u>፡፡» ድመቶች በተፈጥሮ የሚያውቁትንና የሚያደርጉትን ነገር(ከእነርሱ የወጣውን በአፈር መክደን) ሰው ግን እንደ ትእዛዝ ሊነገረው አስፈለገ፡፡

ቁ. 19-20 «ለወንድምህ በወለድ አታበድር … ለእንግዳው በወለድ አበድረው»

ቁ. 21-23 «ለአምላክህ ለእግዚአብሔር ስእለት በተሳልህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ከአንተ ፈጽሞ ይሻዋልና ኃጢአትም ይሆንብሃልና <u>መክፈሉን አታዘግይ … ከከንፈርህ የወጣውን ታደርግ ዘንድ ጠብቅ</u>፡፡»

<u>ከዚህ ክፍል ስለ ስለት የምንማራቸው ነገሮች፡</u> -

1. የተሳልነውን እንድንፈጽም እግዚአብሔር ይጠብቅብናል፡፡
2. ስእለቱን አለመፈጸም ብቻ ሳይሆን <u>ማዘግየትም</u> ኃጢአት ነው፡፡

<u>ዘዳ. 24 - ልዩ ልዩ ማሳሰቢያዎች</u>

ቁ. 1-4 ስለ ፍቺ የተሰጠ መመሪያ
ቁ. 5 አዲስ ሙሽራ ወደ ጦርነት እንዳይሄድ
ቁ. 6-22 የተለያዩ ትእዛዞች

- ለሠራተኛ በወቅቱ ስለ መክፈል
- ለሌሎች ቸርነት ስለማድረግ

<u>ዘዳ. 25፡ - ልዩ ልዩ ትእዛዞች</u>

ቁ. 1-3 አንድ በደለኛ ሰው ስለሚደርስበት ግርፋት (አርባ ጅራፍ የመጣው ከዚህ ክፍል ነው)፡፡

ቁ. 4 «እህል የሚያበራየውን በሬ አፉን አትሰር» በአዲስ ኪዳን ይህ ጥቅስ ለእግዚአብሔር አገልጋዮች ተጠቅሶ እናያለን (1ቆሮ. 9÷9)፡፡

ቁ. 5-10 አንድ ሰው ለወንድሙ ዘርን ማስቀረትና ስሙን ማስጠራት እንዳለበት፡ -

ቁ. 11-19፡ - ልዩ ልዩ ትእዛዛትን ከሰጠ በኋላ፤ ወደ ተስፋይቱ ምድር ሲገቡ አማሌቅን እንዲያጠፉ ያዛቸዋል፡፡ «አንተም ተስኖህ፣ ደክመህ ካለህ ከአንተ በኋላ ደክመው የነበሩትን እንደመታ፤ እግዚአብሔር ባሳረፈህ ጊዜ የአማሌቅን ዝክረ ስሙን ከሰማይ በታች አጥፋው፣ ይህንን አትርሳ፡፡»

<u>ዘዳ. 26</u>፣- ወደ ተስፋይቱ ምድር ገብተው ስለሚያቀርቡት በኩራትና አሥራት፤

ቁ. 2 «ከምትሰበስበው ሁሉ በኩራት ውሰድ ... አምላክህ እግዚአብሔር ስሙ ይጠራበት ዘንድ ወደ መረጠው ስፍራ ይዘህ ሂድ፡፡»

ቁ. 14 ከአሥራታችን ለምንም ጉዳይ መውሰድ እንደሌለብን «<u>በኀዘኔ ጊዜ</u> እኔ ከእርሱ አልበላሁም <u>ለርኩስነቴም</u> ከእርሱ አላወጣሁም፡፡» ለእግዚአብሔር መግባት ያለበትን አሥራት ደስ ሲለን ብቻ ሳይሆን በኀዘናችንም ጊዜ መስጠት አለብን፡፡ ለርኩስነቴም ከእርሱ አላወጣሁም ሲል፤ ለኃጢአትና ለበደል ለሚያቀርቡት መሥዋዕት አሥራታቸውን መስጠት እንደሌለባቸው ማስሰቡ ነው፡፡ አሥራት ራሱን የቻለ ለብቻው መቅረብ ያለበት መሥዋዕት እንደሆነ ያማለክታል፡፡

<u>ዘዳ. 27</u>፡ - ዮርዳኖስን ተሻግረው ወደ ተስፋይቱ ምድር በገቡ ጊዜ ታላላቅ ድንጋዮችን በጌባል ተራራ ላይ ለመታሰቢያ እንዲያቆሙና የእግዚአብሔርን ሕግ እንዲጽፉባቸው ያሳስባቸዋል፡፡

- እግዚአብሔር ሕጉን (ቃሉን) እንድንረሳ ስለማይፈልግ ሁልጊዜ በምናየውና በግልጽ ሁኔታ በዓይናችን ፊት እንድናደርገው ይፈልጋል፡፡

ቁ. 8 «የዚህንም ሕግ ቃሎች ሁሉ የተገለጠ አድርገህ ድንጋዮቹ ላይ ጻፍ።»

- በተጨማሪም በዚህ ተራራ ላይ መሠዊያ እንዲሠሩ ያዛቸዋል። የሙሴ ሕግ ብቻውን ደኅንነትን (ጽድቅን) መስጠት ስለማይችል፣ ከህጉ ጋር አብሮ መሠዊያ መኖር ነበረበት «ደም ሳይፈስ ስርየት የለምና»

ቁ.5-6 በዚያም ለአምላህ ለእግዚአብሔር መሠዊያ ሥራ። መሠዊውያውም ብረት ካልነካው ድንጋይ ይሁን። ካልተጠረበም ድንጋይ የአምላክህን የእግዚአሔርን መሠዊያ ሥራ።» መሠዊው ብረት ያልነካው (ያልተጠረበ) ይሁን ማለቱ፤ ደኅንነት ወይም የኃጢአት ሥርየት በሰው ጥበብና ብልሃት እንደማይመጣ የሚያሳስብ ነው። አዋቂና ጥበበኛ ከጠበረበው ድንጋይ የተሠራውን መሠዊያ እግዚአብሔር አልፈለገም። ይህ መሠዊያ የኢየሱስ ርስቶስን ስለ እኛ መስቀል ላይ መሠዋት ያሳስበናል። የመስቀሉ (የመሠዊያው) ቃል ለሚጠፉት ሞኝነት ለእኛ ለምንድን ግን የእግአብሔር ኃይል ነውና። የጥበበኞችን ጥበብ አጠፋለሁ፣ የአስተዋዮችንም ማስተዋል እጥላለሁ ተብሎ ተጽፎአልና» (1ቆሮ. 1፥18-19)።

ለእግዚአብሔር የምናቀርበውም መሥዋዕት እኛ ጥበብና ማስተዋል የመነጨ ሳይሆን ከመንፈስ ቅዱስ የሆነ ብቻ መሆን እንዳለበት ያመለክተናል። እኛ ጥበብ የተጠረበውን ድንጋይ እግዚአብሔር አይፈልግም።

ቁ. 11-26 12ቱ ነገዶች ለሁለት ተከፍለው፤ 6ቱ ከገሪዛን ተራራ ላይ 6ቱ ደግሞ በጌባል ተራራ ላይ ቆመው በረከትንና እርግማንን በረከቱ ደግሞ ጌባል ተራራ ላይ ቆመው በረከትንና እርግማንን ያስተላልፋሉ (ዘዳ.11፥2-29 ላይ ተመልከት)። በረከቱ የእግዚአብሔር ትእ ከተላለፉ ነው። እርግማኑና በረከቱ ምዕ. 27 ቁ. 15 ጀምሮ እስከ ምዕ. 28 መጨረሻ ይሄዳል።

ዘዳ. 28 - የእግዚአብሔርን ቃል በመስማትና በማድረግ የሚመጣውን በረከት 1-14 ይዘረዝራል የእግዚአብሔርን ቃል በመተላለፍ የሚመጣውን እርግማን ደግሞ ከቁ 15-68 ይዘረዝራል።

የእርግማኑ ርዝመት ከበረከቱ ይልቅ ከሦስት እጥፍ በላይ ነው (በረከቱ 14 ጥቅስ እርግማኑ 53 ጥቅስ)።

ቁ. 1ሀ እንዲህም ይሆናል ...»፤ ይህ ቃል፣ ትንቢታዊ የሆነ መልዕክት እንደሚከተል ያሳያል። «ሆኗል» ወይም «እየሆነ ነው» አይልም፤ ነገር ግን «ይሆናል» በማለት የወደፊትን ጊዜ ያመለክታል።

ቁ. 1ለ የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ ..» ሲል፣ እግዚአብሔር በመጀመሪያ ከእኛ የሚፈልገው ቃሉን እንድንሰማ እንደሆነ ሲያመለክት ነው። መክ. 5፥1 ... ለመስማት መቅረብ ከሰነፎች መሥዋዕት ይበልጣልና» የሚል ቃል እናገኛለን፤ (ቃሉን) ለመስማት መቅረብ ራሱ መሥዋዕት ነው። የሚሰማኝ ግን በእርጋታ ይቀመጣል ከመከራም ሥጋት ያርፋል» (ምሳሌ 1፥33)።

እግዚአብሔር አስቀድሞ ... የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ» ያለው። እምነት ከመስማት መስማትም ከእግዚአብሔር ስለሆነ ነው (ሮሜ 10፥17)። መስማት ከሌለ መታዘዝ አይኖርም። ... ማዳመጥ የአውራ በግ ስብ ከማቅረብ ይበልጣል። (1ኛ. ሳሙ 15፥22)።

ቁ. 1ሐ ... ዛሬ ያዘዝሁን ትእዛዙን ሁሉ ብታደርግ» የሚቀጥለው ትእዛዝ አድርግ ነው። ሰምተን እንዳልሰማ ሰው ቁጭ ማለት እንችላለን። ከሰማን በኋላ በሰማነው ቃል በምናገኘው እምነት የሰማነውን ቃል በተግባር መግለጽ አለብን። «እምነት ያለ ሥራ የሞተ ነውና (ያዕ. 2፥17)። ቃሉን የምታደርጉ ሁኑ እንጂ ራሳችሁን እያሳታችሁ የምትሰሙ ብቻ አትሁኑ። ቃሉን የሚሰማ የማያደርገውም ቢኖር የተፈጥሮ ፊቱን በመስተዋት የሚያይን ሰው ይምስላል፤ ራሱን አይቶ ይሄዳልና ወዲያውም እንደምን እንደሆነ ይረሳል። ነገር ግን ነፃ የሚያወጣውን ፍጹሙን ሕግ ተመልክቶ የሚጸናበት፣ ሥራንም የሚሠራ እንጂ ሰምቶ የሚረሳ ያልሆነው በሥራው የተባረከ ይሆናል» (ያዕ. 1፥22-25)።

ቁ. 1መ ... ብትጠብቅም ...» ከመስማትና ከማድረግ ቀጥሎ የሚጠብቅን ትእዛዙን (ቃሉን) መጠበቅ ነው። አንድ ጊዜ አድርጎ ማቆም ይቻላል። መጠበቅ ግን ጽናትንና ትጋትን ያመለክታል። የእግዚአብሔርን ቃል ሲመችን ማድረግ ሳይመቸን ደግሞ መተው ሳይሆን ጸንተን መጠበቅ እንዳለብን ያሳስበናል። ዳዊት፤ አንተን እንዳልበድል ቃልህን በልቤ ሰወርኩ» እንዳለ እኛም ቃሉን ጸንተን መጠበቅ አለብን።

እንዲሁም (መዝ. 118 (119)፣ 60) ትእዛዝህን ለመጠበቅ ጨከንኩ አልዘገየሁምም» ይላል። የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመጠበቅ አንዳንድ ጊዜ መጨከንና መፍጠን ያስፈልጋል።

ከቁ. 1-14 የሚናገረው፡ - ቃሌን ከሰማህ፣ ካደረግህና ከጠበቅህ .. እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል፣ ያገኙህማል፡፡(ቁ. 2) … እግዚአብሔር በረከቱ በአንተ ላይ ጎተራህ ላይ በእጅህም ሥራ ሁሉ እንዲወርድ ያዝዛል… (ቁ. 8) … መልካሙን መዝገብ ከሰማይን ይከፍትልሃል (ቊ. 12) …»

በአጻንሩ ደግሞ፡ - ቁ. ከ15-68

«የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ባትሰማ … ባትጠብቅ ባታደርግም እነዚህ መርገሞች ሁሉ ይመጡብሃል ያገኙህማል …» በማለት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ካመጹ የሚደርስባቸውን ቅጣት ይዘረዝራል፡፡ የተዘረዘውን እርግማን እንኳን በሕይወት ለመለማመድ ማንበቡ እንኳን ያሰቅቃል፡፡

- ከዚህ ክፍል አንድ ሳንጠቅስ ማለፍ የሌለብን ቃል አለ፤

  ቁ. 47 «ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍስሐና በሐሴት አላመለክህምና» በማለት፤ እግዚአብሔርን በደስታ (በምሥጋና) አለማምለክ ራሱ ኃጢአት እንደሆነ ያሳስበናል፡፡

ይህ ክፍል፤ …ለጠላቶቻችሁ ራሳችሁን ትሸጣላችሁ የሚገዛችሁም አይገኝም፡፡» በማለት እግዚአብሔርን አለመስማትና አለመታዘዝ የሚያመጣውን ውርደት በመናገር ይደመድማል፡፡

ዘዳ.29፡ - ለአዲሱ ትውልድ ሙሴ ተጨማሪ ማስጠንቀቂያና ማሳሰቢያ ይሰጣቸዋል፡፡

በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ ሙሴ አንድ ጠቃሚ ቃል አስፍሮልናል፤ ምስጢሩ ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ነው፤ የተገለጠው ግን የዚህን ሕግ ቃሎች ሁሉ እናደርግ ዘንድ ለእኛ ለዘላለምም ለልጆቻችን ነው» (ቁ. 29)፡፡

ከዚህ ቃል የምንረዳው፤ ሁልጊዜ ምስጢር የሚሆንብን ነገር አለ፤ የተገጸለልን ነገር ደግሞ አለ፡፡ ምስጢር የሆነብንን ነገር እግዚአብሔር ፈቃዱ ከሆነ እስኪገልጥልን ድረስ ለእግዚአብሔር መተው ይኖርብናል ለተገለጠልን እውነት ግን መመላለስ ይኖርብናል፡፡ ለተገለጠልንና ለተረዳነው እውነት ተጠያቂዎች ነን፡፡

ዘዳ.30፡ -እግዚአብሔር የሚምርና የሚራራ አምላክ ስለሆነ የእግዚአብሔርን ቃል ባለመስማትና ባላማድረጋቸው በምዕ. 28 የተጻፈው እርግማን ከደረሰባቸው በኋላ እንኳን በፍጹም ልባቸው ቢመለሱ እግዚአብሔር እንደሚምራቸውና እንደሚባርካቸው ይናገራል፡፡

ቁ. 1-3 እንዲህም ይሆናል እኔ በፊትህ ያኖርሁት ነገር ሁሉ፣ በረከቱና መርገሙ በወረደብህ ጊዜ ... ወደ አምላክህ ወደ እግዚአብሔር ተመልሰህ ... በፍጹም ልብና በፍጹም ነፍስህ ለቃሉ በታዘዝህ ጊዜ አምላክህ እግዚአብሔር ምርኮህን ይመልሳል፣ ይራራልህማል፣ አምላክህም እግዚአብሔር አንተን ከበተነበት አሕዛብ ሁሉ መካከል መልሶ ይሰበስብሃል፡፡»

ቁ. 11-14 -የእግዚአብሔር ትእዛዝ ሰማይን ቧጥጠን የምናወርደው ወይም ከባህር ማዶ ተሻግረን የምናመጣው ሳይሆን፤ ታደርገው ዘንድ ቃሉ በአፍህና በልብህ ውስጥ ለአንተ እጅግ ቅርብ ነው» ይለናል፡፡

ቁ. 15-20 -እግዚአብሔር በፊታችን ሕይወትንና ሞትን እንዳስቀመጠና ህይወትን መምረጡ የእኛ ፈንታ እንደሆነ ይናገራል፡፡

እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፡፡ እርሱ (እግዚአብሔር) ሕይወትህ የዘመንህም ርዝመት ነውና አምላክህን እግዚአብሔርን ትወድደው ትጠባበቀውም ቃሉንም ትሰማ ዘንድ ምረጥ፡፡»

ዘዳ. 31፡ - ከቁ. 1-13፤ ሙሴ ለእስራኤልና ለኢያሱ የሚናገረው የማበረታቻ ቃል ሲሆን፤ ቁ. 14-23፡ -እግዚአብሔር ሙሴንና ኢያሱን ጠርቶ ለእነርሱና ለሕዝቡ የሚሆን ቃል ይናገራቸዋል፡፡

ቁ. 14 እግዚአብሔርም ሙሴን፡ - የምትሞትበት ቀን እነሆ ቀረበ ይለዋል፡፡ አብዛኛውን ጊዜ የእግዚአብሔር ሰዎች የሚሞቱበት ቀን ሲደርስ እግዚአብሔር ያስታውቃቸዋል፡፡ መጨረሻ ላይ ማድረግ ያለባቸውን ነገር እንዲያጠናቅቁ ማሳሰቢያ መስጠቱ ነው፡፡ ጴጥሮስ 2ጴጥ.1÷14 «ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዳመለከተኝ ከዚህ ማደሪያዬ መለየቴ ፈጥኖ እንዲሆን አውቃለሁና» ይላል፡፡ ጳውሎስም 2ጢሞ. 4÷6 «በመሥዋዕት እንደሚደረግ የእኔ ህይወት ይሠዋልና፣ የምሄድትም ጊዜ ደርሶአል፡፡» ይላል፡፡ ንጉሡ ሕዝቅያስንም

እግዚአብሔር፤ «ትሞታለህ እንጂ በሕይወት አትኖርምና ቤትህን አስተካክል» (2ኛ ነገ.20፥1) ብሎ ሲያሳስበው እናነባለን፡፡ ሙሴንም በዚህ ክፍል እንዲሁ ሲያሳስበው ነው የምናየው፡፡

በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ኢያሱን የእስራኤልን ልጆች ወደ ማልሁላቸው ምድር ታገባላህና ጽና አይዞህ፣ እኔም ከአንተ ጋር እሆናለሁ» ብሎ ያዘዋል (ቁ.23)፡፡

በተጨማሪም እግዚአብሔር ስለ ሕዝቡ አመፅኝነት ከተናገረ በኋላ፣ ወደፊት እኔን ክደው ወደ ሌሎች አማልክት ሲሄዱ ምስክር ትሆንባቸው ዘንድ ይህችን መዝሙር አስተምሯቸው ብሎ ለሙሴና ለኢያሱ አንድ መዝሙር ይሰጣቸዋል፡፡ ይህንን መዝሙር በምዕ. 32 ላይ ተጽፎ እናገኘዋለን፡፡

(ቁ.21) «ዛሬ፣ ወደማልሁላቸው ምድር ገና ሳላገባቸው የሚያስቡትን አሳብ አውቃለሁና»፤ ዛሬ የምናስበው ሐሳብ ነገ የምንደርስበትን ቦታ ይወስናል፡፡ ዛሬ በልባችን በሐሳብ መልክ ያለው ነገር በተግባር ተገልጾ ይወጣል፡፡

(ቁ.29) ሙሴም፤ «... በእግዚአብሔር ፊት ክፉ ስላደረጋችሁ በኋለኛው ዘመን ክፉ ነገር ያገኛችኋል» ይላቸዋል፡፡ «ሰው ሁሉ የዘራውን ያንኑ ደግሞ ያጭዳልና» ተብሎ እንደተጻፈው በእግዚአብሔር ፊት ክፉን የሚያደርግ ሁሉ ቢዘገይም እንኳን ክፉን (የዘራውን) ማጨዱ አይቀርም፡፡ «በእግዚአብሔር ፊት» ሲል፤ የምንሠራው ሁሉ ከእርሱ እይታ የተሠወረ አለመሆኑን ሲያሳየን ነው፡፡ ዮሴፍ በጶጢፋር ሚስት በተፈተነ ጊዜ፡ - «እንዴት ይህን ትልቅ ክፉ ነገር አደርጋለሁ? <u>በእግዚአብሔር ፊት</u> እንዴት ኃጢአትን እሠራለሁ?» አለ፡፡

<u>ዘዳ 32</u>፡ - እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን ምስክር ትሆን ዘንድ የሰጣት መዝሙር፡፡ በመዝሙሩ ውስጥ፤

- የእግዚአብሔርን ቀናነትና የሕዝቡን ጠማማነት፤
- እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ታማኝነት እና እንክብካቤ፣ የሕዝቡን ደግሞ ዓመጽና አለማስተዋል እናያለን፡፡

ቁ. 4 «እርሱ አምላክ ነው፤ ሥራውም ፍጹም ነው፤ <u>መንገዱም ሁሉ የቀና ነው፡፡</u>

ቁ..5 «እነርሱ ረከሱ ልጆቹም አይደሉም ነውርም አለባቸው፤ <u>ጠማማና ገልበጥባጣ ትውልድ</u> ናቸው፡፡»

ቁ.9 «<u>የእግዚአብሔር ዕድል ፈንታ ሕዝቡ ነው</u>፤ ያዕቆብም የርስቱ ገመድ ነው።» በመዝሙረ ዳዊት «<u>እግዚአብሔር ዕድል ፈንታዬ ነው</u>» ይላል (መዝ. 142፥5፤ 119፥57፣ 73፥26) በዚህ ክፍል ግን «የእግዚአብሔር ዕድል ፈንታ ሕዝቡ ነው» ይላል። እግዚአብሔር ዕድል ፈንታችን እንደሆነ ሁሉ፤ እኛም ለእግዚአብሔር ዕድል ፈንታው ነን። ማለትም፤ ሐሳቡን፣ ዓላማውንና፣ የዘላለም ዕቅዱን የሚያከናውነው በሕዝቡ በኩል ነው።

<u>ስለ እግዚአብሔር ልዩ ጥበቃ እንዲህ ይላል፤</u>

ቁ. 10 «በምድረ በዳ በጥማት የነፍስ ጩኸትም በሞላበት ውድማ አገኘው ከበበው ተጠነቀቀለትም፤ <u>እንደ ዓይን ብሌን</u> ጠበቀው።»

ቁ. 36 «ኃይላቸው እንደ ደከመ
የተዘጋ የተለቀቀም እንደሌለ ባየ ጊዜ፤
እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳል
ስለ ባሪያዎቹም ያዝናል።»

እግዚአብሔር በራሳችን ኃይል ከመታመን እስከምንደክምና ያለ እርሱ ዕድል ፈንታ እንደሌለን እስከምንረዳ ይጠብቃል፤ ያን ጊዜ ስለ እኛ ያዝናል፣ ይራራልናል።

<u>በአንጻሩ ደግሞ ስለ ሕዝቡ አለመታመን እንዲህ ይላል፤</u>

ቁ. 15 «ይሹሩን (እስራኤል) ወፈረ፤ ረገጠ፤ ወፈረ፣ ደነደነ፣ ሰባ
የፈጠረውንም እግዚአብሔርን ተወ።»

ቁ. 28-29 «ምክር ያጡ ሕዝብ ናቸው፣
ማስተዋልም የላቸውም።
አእምሮ ቢኖራቸው፣
ይህንን ያስተውሉ ነበር
ፍጻሜያቸውንም ያስተውሉ ነበር።»

ቁ. 48-52 እግዚአብሔር ሙሴን ወደ ተራራው ውጣ በወጣህበትም ተራራ ሙት ብሎ ሲያዘው እናያለን። «በሞዓብ ምድር በዓባራም ተራራ ውስጥ ወዳለው ወደ ናባው ተራራ ውጣ ለእስራኤልም ልጆች ርስት አድርጌ የምሰጣቸውን የከነዓንን ምድር እይ ወንድምህም አሮን በሖር ተራራ እንደ ሞተ ወደ ወገኖቹም እንደተከማቸ በወጣህባት ተራራ ሙት ወደ ወገኖችህም ተከማች።»

ዘዳ.33- ሙሴ ሳይሞት እሥራኤላውያንን የባረከባትን በረከት ይዘረዝራል፡፡

- ከዚህ ምዕራፍ የምንማረው፤ የእግዚአብሔር ሰዎች በእነርሱ ኃላፊነት ሥር ያሉትን ሰዎች ከባረኩ በኋላ ነው የሚሰናበቱት፡፡ በዘፍ. 49 ላይ ያዕቆብ 12ቱን ልጆቹን ጠርቶ ሲባርካቸው እናነባለን፡፡

ከዘዳግም 33 ውስጥ በጣም የሚያስገርመው ነገር ከ12ቱ ነገዶች መካከል ስምዖን አለመኖሩ ነው፡፡ በዘፍ. 49 ላይ ያዕቆብ ልጆቹን በባረከበት በረከት ውስጥ ተጠቅሶ እናገኘዋለን፡፡ በዘህ ምዕራፍ ግን ስሙም አልተጠቀሰም፡፡ ምክንያቱን ብንመረምር በዘኍልቍ 25 ላይ ሕዝቡ ከሞዓብ ልጆች ጋር ሲያመነዝሩና ፊንሐስ (የአሮን የልጅ ልጅ )በእጁ ጦር ይዞ አንዱን እሥራኤላዊና አንዲት ምድያማዊት ሴት በጦር ሆዳቸውን በመውጋት የእግዚአብሔርን ቅንዓት ሲያሳይና መቅሠፍቱ በእርሱ ምክንያት ሲከለከል አይተናል፡፡ በዘኍ. 25÷14፤ ላይ የተገደለው እስራኤላዊ የስምዖን ትወልድ በ63% ቀንሶ እንደነበረ፣ተሚልከተናል፡፡ከግብጽ ከወጣው ሕዝብ መካከል የስምዖን ቁጥር 59,300 ሲሆኑ (ዘኍ. 1÷23) በአዲሱ ቆጠራ ግን 22,200 ብቻ ነበረ( ዘኍ. 26÷14)፡፡ ይህ የቁጥር ማነስ በዘኍልቁ ምዕራፍ 25 ላይ በነበረው ዓመጽ ዋና ዋናዎቹ የስምዖን ወገኖች እንደነበሩና በመቅሠፍት ያለቁትም አብዛኞቹ እነርሱ እንደሆኑ በዘኍልቁ መጽሐፍ ጥናት ላይ ጠቅሰናል፡፡ በዘዳግም.33 ላይ የስምዖን ስም አለመጠቀሱ ስናይ ደግሞ የዘኍል.25 ዓመጽና መቅሠፍት አሁንም በረከት አልባ ያደረጋቸው መሆኑን እናያለን፡፡ ከጊዜ አንፃር ስናየው በዘኍ. 25 እና በዘዳ. 33 (የሙሴ የመጨረሻ ባርኮት) መካከል የጥቂት ወራት ልዩነት ስለሆነ የስምዖን ዓመጽ በእግዚአብሔርም ዘንድ ሆነ በሙሴ ወይም በእስራኤዊያን ዘንድ ገና ትኩስ ነበረ (አልተረሳም)፡፡

ከዚህ ምዕራፍ የምናስተውላቸው ሌሎች ነጥቦች፤ በቁ. 4 «<u>ሙሴ ለያዕቆብ ጉባኤ ርስት የሆነውን ሕግ</u> አዘዘን» ይላል፡፡ እግዚአብሔር የሰጠው ሕግ ራሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ <u>ርስት</u> ነበረ፡፡ እስራኤላወያን ወተትና ማር የምታፈሰውን ርስት ከመውረሳቸው በፊት የእግዚአብሔርን ሕግ መውረስ ነበረባቸው፡፡ የቀድሞው ትውልድ (ከግብጽ ባርነት የወጣው) የተስፋይቱን ምድር መውረስ ያልቻለው፤ የእግዚአብሔርን ሕግ በሙሉ ልብ ስላልወረሰ ነበረ፡፡ የእግዚአብሔርን ሕግ የወረሰው ትወልድ ግን የተስፋይቱንም ምድር ወረሰ፡፡ ዳዊት በመዝ. 118÷(119)÷111 እንዲህ ይላል «የልቤ ደስታ ነውና <u>ምስክርህን </u>(ሕግህን፣ ቃልህን) <u>ለዘላለም ወረስሁ</u>»

ሌላ የምናስተውለው ነገር፡ - <u>የሌዊና የዮሴፍ በረከት</u> ዝርዝር መርዘሙን ነው:: እነዚህ ሁለት ወገኖች ለእግዚአብሔር ሕዝብ (ለእስራኤል) ትልቅ ውለታ ያደረጉ ናቸው:: ዮሴፍ ራሱን መሥዋዕት አድርጐ እስራኤልን (አሕዛብንም ጭምር) ከረሃብ ያተረፈ ነው፤ የሌዊ ወገን ደግሞ፤(ሙሴንና አሮንንም ይጨምራል) እስራኤልን በክህነት ያገለገለ፣ ምድራዊ ርስት ሳይካፈል እግዚአብሔር ራሱ ርስቱ የሆነ ወገን ነበረ:: በተጨማሪም እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ ሠርተው ባመጹ ጊዜ ሙሴ በዘጸ. 32÷26 «... የእግዚአብሔር ወገን የሆነ ወደ እኔ ይምጣ አለ፤ የሌዊም ልጆች ሁሉ ወደ እርሱ ተሰበሰቡ::» ከዚያም በእግዚአብሔር ትእዛዝ ወንድሞቻቸውን (የወርቁን ጥጃ ያመለኩትን) በሰይፍ እንደገደሉ እናያለን (ዘጸ. 32÷27-29):: ይህንን ታሪክ በማስመልከት ነው በዘዳ. 33÷9 ላይ «... ወንደሞቹንም ላላስተዋ...» የሚል ቃል የምናነበው:: «ወንድሞቼ ናቸው» ብሎ አመጸኞችን ከመግደል ወደ ኋላ አላለም ማለት ነው:: በተጨማሪም፤ «ቃልህን አደረጉ፣ ቃል ኪዳንህንም ጠበቁ ይላል::

ከሌሎቹ ነገዶች በረከት ውስጥ <u>የብንያምን በረከት</u> ስናይ እግዚአብሔርን ለሚወድ ሰው ሁሉ እንደሆነ እናስተውላለን::

ቁ. 12 «... በእግዚአብሔር የተወደደ በእርሱ ዘንድ ተማምኖ ይኖራል፤ ቀኑን ሁሉ ይጋርደዋል፣ በትከሻውም መካከል ያድራል::»

በመጨረሻ፣ ከቁ. 26-29 ለእስራኤል ሁሉ የሚሆን አጠቃላይ በረከት ይናገራል::

እስራኤልን ወይም ያዕቆብን፡ - «ይሹሩን» ይለዋል::

«ይሹሩን ሆይ (ያዕቆብ ሆይ) በሰማያት ላይ ለረድኤትህ፡ - በደመናትም ላይ በታላቅነት እንደሚሄድ እንደ እግዚአብሔር ያለ ማንም የለም:: መኖሪያህ የዘላለም አምላክ ነው የዘላለም ክንዶች ከአንተ በታች ናቸው፣ ጠላትህን ከፊትህ አውጥቶ አጥፋው ይላል፤ <u>እስራኤልም</u> ተማምኖ የያዕቆብም ምንጭ ብቻውን እህልና የወይን ጠጅ ባለባት ምድር ይኖራል፤ ሰማያቱም ጠልን ያንጠባጥባሉ:: <u>እስራኤል</u> ሆይ ምስጉን ነህ፣ በእግዚአብሔር የዳነ ሕዝብ እንደ አንተ ማን ነው? እርሱ የረድኤትህ ጋሻ የከፍተኛነትህም ሰይፍ ነው:: ጠላቶችህም ይገዙልሃል አንተም ከፍታቸውን ትረግጣለህ::»

ዘዳ. 34፡ - ሙሴ የተስፋይቱ ምድር ካየ በኋላ በተራራው ላይ እንደሞተ፣ እስራኤልም ለሠላሳ ቀን እንዳለቀሱለት ይገልጻል።

በቁ. 9 ላይ ሙሴ ከመሞቱ በፊቱ «እጆቹን ስለጫነበት የነዌ ልጅ ኢያሱ የጥበብን መንፈስ ተሞላ የእስራኤልም ልጆች ታዘዙለት» በማለት በእጅ መጫን የእግዚአብሔርበረከት(የእግዚአብሔር መንፈስ) እንደሚተላለፍ ያሳየናል።

ቁ. 7፡ - ሙሴ በ120 ዓመቱ ሲሞት ዓይኑ አልፈዘዘም፣ ጉልበቱ አልደነገዘም ይላል። በእግዚአብሔር ጥበቃ ውስጥ ከሆን፣ ልናረጅ፣ ልንሸመግል እንችላለን፤ ነገር ግን አንጃጅም። ዳዊት፤ «ሽምግልናዬም በዘይት ይለመልማል» (መዝ. 92÷10)።

በመጨረሻም፤ «እግዚአብሔርን ፊት ለፊት እንዳወቀው እንደ ሙሴ ያለ ነቢይ ከዚያ ወዲህ በእስራኤል ዘንድ አልተነሣም ... ምልክትና ድንቅ ያደርግ ዘንድ እግዚአብሔር እንደላከው ያለ በእስራኤል ሁሉ ፊት በጸናች እጅ ሁሉና በታላቅ ማስደንገጥ ሁሉ እንዳደረገው እንደ ሙሴ ያለ አልተነሣም።» በማለት የሙሴን ታላቅነት በመግለጽ ይደመድማል።

# ምዕራፍ ስድስት፣ ጥያቄዎች

1. ዘዳግም በስንት ክፍሎች ይከፈላል? ክፍሎቹንና ንዑስ ክፍሎቹን ጥቀስ፡፡
2. የዘዳግም መጽሐፍ በአጠቃላይ የሚያመለክተው ምንድን ነው?
3. ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዲያብሎስ ሲፈተን ሦስቱንም ጊዜ የጠቀሰው ከዘዳግም እንደሆነ አይተናል፡፡ እነዚህ ሦስት ጥቅሶች ምን ይላሉ?
4. በዘዳግም 17 ላይ አንድ ንጉሥ (መሪ) ማድረግ ያለበትንና የሌለበትን ነገሮች ይዘረዝራል፡፡ እነዚህ ነገሮች ምንድን ናቸው? በመንፈሳዊ አመራር ላይ ላለስ ሰው ምን ትምህርት አላቸው?
5. በዘዳግም 28 ላይ፤የእግዚአብሔር ቃል ብትሰማ … ብታደርግ… እና ብትጠብቅ… በአንፃሩ ደግሞ ባትሰማ … ባትጠብቅና … ባታደረግ … የሚሉ ቃላት አሉ፡፡ እነዚህ ቃላትና ከእነርሱ ጋር አብሮ የተጻፈው በረከትና መርገም ላንተ ምን ትርጉም አለው?
6. በዘዳግም 33 ላይ ሙሴ ከመሞቱ በፊት እስራኤልን ሲባርክ ከ12ቱ ነገዶች በረከት ያልተቀበለው ነገድ ማነው? በቀጥታ ባይገለጽም፣ በረከት ያልተቀበለበት ምክንያት ምን ይመስልሃል? ይህስ ምን ያስተምረናል?
7. ሙሴ 12ቱን ነገዶች ሲባርክ በተለይ የሌዊና የዮሴፍ በረከት ልዩ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ የእነዚህ ሁለት ነገዶች በረከት ልዩ የሆነበትን ምክንያት በተናጥል አስረዳ፡፡
8. በዘዳግም 33፥26-29 በአጠቃላይ ለእስራኤል(ለእግዚአብሔር ሕዝብ) ከተሰጠው በረከት ውስጥ፤ አንተ እንደ እግዚአብሔር ሰው ይህንን በረከት ለግልህ የምትቀበለው እንዴት ነው? ክፍሉን ደግመህ ካነበብህ በኋላ ከሕይወትህ ጋር በእምነት ያዋሃድከውን (የተቀበልከውን) ብቻ ጥቀስ፡፡